# እሰይ ተነሳ

እሰይ ተነሳ እሰይ እሰይ ተነሳ (፪)
ተደመሰሰ ባምላክ የአለም አበሳ (፪)

| | | |
|---|---|---|
| ክብርና ምስጋና | እሰይ | እሰይ ተነሳ |
| ይግባው ፈጣሪያችን | እሰይ | እሰይ ተነሳ |
| ሞትን ድል አድርጎ | እሰይ | እሰይ ተነሳ |
| አርአያ የሆነን | እሰይ | እሰይ ተነሳ |

አዝ...

| | | |
|---|---|---|
| በከርሰ መቃብር | እሰይ | እሰይ ተነሳ |
| ሶስት ቀን ሶስት ሌሊት | እሰይ | እሰይ ተነሳ |
| ተቀብሮ አልቀረም | እሰይ | እሰይ ተነሳ |
| ተነስቷል በሰንበት | እሰይ | እሰይ ተነሳ |

አዝ...

| | | |
|---|---|---|
| ለሐዋርያቶች | እሰይ | እሰይ ተነሳ |
| የምስራች ያለች | እሰይ | እሰይ ተነሳ |
| ማርያም መግደላዊት | እሰይ | እሰይ ተነሳ |
| ምንኛ ታደለች | እሰይ | እሰይ ተነሳ |

አዝ...

| | | |
|---|---|---|
| ዘበኞች ቢያቆሙ | እሰይ | እሰይ ተነሳ |
| አይሁድ ተሞኝተው | እሰይ | እሰይ ተነሳ |
| አልቻሉም ሊያስቀሩት | እሰይ | እሰይ ተነሳ |
| ሞትን ድል አረገው | እሰይ | እሰይ ተነሳ |

አዝ...

www.HolyTrinityEOTCNY.org